# ቀስተ ደመና

የሰላምና የወድማማችነት ድምፅ ሬድዮ ጋዜጣ

ቁጥር 1-3 ልዩ እትም መስከረም / ህዳር 1990

## ከአዘጋጅ ብዕር

መስከረም 1 ቀን 1990 ዓ ም ሥርጭቱን የጀመረው የቀስተ ደመና ሬዲዮ፤ የሰላምና የወንድማማችነት ድምፅ የአራት ወራት የአገልግሎት ግዜውን አጠናቅቆ አምስተኛ ውን ወር ሊይዝ ነው።

የቀስተ ደመና ሬዲዮ የሚያስተላልፋቸው ዜናዎች ፤ ትችቶችና ትንተናዎች ፤ ቃለ መጠይቆች ወዘተ በአየር ላይ ውለው ሳይጨበጡ እንደተበተኑ የትም እንዳይቀሩና በፅሁፍ ተቀርፀው ቢቀመጡ ለተደራሲው የሚሰጡት ጥቅም የላቀ ይሆናል ብለን በማሰብ ፤ ከወራት በፊት አንድ መፅሄት ለመጀመር አቅደን ጊዜ ጊዜን እየወለደ ዛሬ ላይ ደርሰናል።

ባለፉት አራት ወራት ቀስተ ደመና ሬዲዮ ያስተላለፋቸውን ትችቶችና አስተያየቶች በማቀናበር ይህንን ‘ልዩ እትም’ አዘጋጅተናል። የተለያዩ ለሃገራችን ወቅታዊ ጉዳዮችና ጥያቄዎች ቅድሚያ ትኩረት የሰጡት እነዚህ አስተያየቶች በርካታ ቁም ነገሮች ያስጨብጣሉ የሚል ዕምነት አለን።

የ ‘ቀስተ ደመና’ ጋዜጣ ከዚህ ልዩ እትም በኋላ በየግዜው እንደሚወጣ ልናበስር እንወዳለን።

መልካም ንባብ !


* የኢሃደግን ጦር ጠማሽ አቋም ላለማገዝ............
ሰላማዊውን የፖለቲካ ትግል አለማፍዘዝ......................................4

* የቡድን ውኅኅንብር ጠቃሚነቱ ለአምባገነኖች ብቻ ነው ................10

* ከፓሪሱ ጉባዔ ያልተቀሰመው ትምህርት..................................3

* ከዶላር ወይስ ከናቅፋ ከጽድቅ ወይስ ከኩነኔ....................9

* ለብቸኛው ልዕለ ኃያል የሚሳነው ነገር አለ ለካ ሄ ሄ.....13

* በነ ዶር ታዬ ላይ በሃሰት አልመሰክርም በማለት ራሳቸው በሃሰት የተወነጀሉት ....................15

* ከባሻገሩ ሽግግሩ እንዳያስቸግር..18

* ለነፃ ምርጫ አመች የኃይል ሚዛን መታገል አንገብጋቢ ጥያቄ ነው ...............................................6

ቀስተ ደመና ሬዲዮ የሚተላለፍበት ፕሮግራም ገጽ.....................................19



አስተያየት፤ ትችት፤ ወዘተ ካላችሁ አድራሻችን እንደሚከተለው ነው፤

Radio Rainbow
c/o P.O.Box 140104
53056 Bonn , Germany . Fax : 0049 228 612381



GRAPECA ሰኢአቀ RAGPEHA

Groupe de Recherche et d'Action pour la pain en Ethiopie et dans la Corne de l' Afrique

Research and Action Group for peace in Ethiopia and the Horn of Africa

ሰላም ለኢትዮጵያና አፍሪካ ቀንድ የምርምርና የተግባር ቡድን

በአለፉት ወራቶች "NEW-AFRICA" የሚባል መጽሄት የወያኔና የሻቢያ መሪዎች +150 የሚለውን ቁጥር የጻፈው+ የዲግሪ ትምህርት ጀመሩ ሲል አብዛኛዎቹ በ "Business administration" "በንግድ ትምህርት ላይ አትኩረዋል" ሲል ለምን እንደሆነ አንባቢዎች ግራ ተጋብተው ነበር። መልሱ ግን ይህ ነው። ሰዎቹ ቱጃርነቱን መርጠዋል። በአውሮፓ አንድ ፖለቲከኛ ፤ አንድ መሪ፤ ፊቱን ወደ ንግድ ከአዞረ የግድ እሱ ብቻ መሆን የለበትም እገሌ ኩባንያው ፤ የሚባል ስም ይሰጠዋል። አቶ መልስና አቶ ኢሳይያስም ለዚሁ መጠሪያ ታድለዋል። አንድ ጸሃፊ ከዚሁ ተነስቶ ጠቅላይ ሚንስትሩና ኩባንያቸው፤ ብሎ ቢጽፍ ምንም አያስገርምም። ........ይገባቸዋል ////

# ትችት፥ ጥንቱን ባልዘፈንሽ ፤ ከዘፈንሽ ባላሳፈርሽ

ባለፍው ሚያዝያ ወር በታላቋ ብሪታንያ በተደረገው አጠቃላይ ምርጫ ሳቢያ በአሸናፊነት የወጣው ሌበር ፓርቲ ሥልጣኑን ሲረከብ እንግሊዝ ከእንግዲህ የምትከተለው የውጭ ፖሊሲ ፍትሃዊ እንደሚሆን ለሰው ልጅ መብት መከበር ቅድሚያ እንደሚሰጥ የተጠበቀ ነበር። በእርግጥም አዲሱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተከበሩ ሮቢን ኩክ ይህንኑ አስመልክተው ለፓርላሜንቱ በሰጡት መግለጫ ከእንግዲህ የሚከተሉት የውጭ ፖሊሲ በሞራልና ስነ ምግባር መርሆዎች ላይ የተመረኮዘ በያለበትም ከሰው ልጅ መብቶች መከበር ቅድሚያ ይሰጣል ሲሉ ምንም እንኳን አንዳንዶች ይህንን አባባል የተለመደ የአዲስ መንግሥት ዲስኩር ነው ብለው ከቁም ነገር ባይቆጥሩትም ብዙዎቹ አመኗቸው።

ብዙም ሳይቆይ የታላቋ ብሪታንያ የቀድሞው መንግሥት ብዙ ታዛቢዎችን ያስገርም የነበረውንና በኢትዮጵያም ህዝብ ፊት ትዝብት ላይ ጥሎት የነበረውን በግፈኛነቱና በሰው ልጅ መብት ረገጣው በአፍሪካም ሆነ በቀረው አለም አሳፋሪ የሆነውንና አንደኛ ቦታ የያዘውን የአህአደግን ፖሊስ የማሰልጠኑን ውል በአቶ አሰፋ ማሩ በግፍ መገደል ሳቢያ ሲያቋርጡ በብዙ ኢትዮጵያን ዘንድ ዲስኩርና ተግባር አንድ ሆኑ የሚል ስሜት አሳድሮ ነበር ።

በዚህን ወቅት የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ተጠሪ በዚች አገር ላለው የፖሊስ ስልጠናው ትብብር ከሰኔ 5 ቀን 1989 ጀምሮ መቋረጡን ሲያስታውቅ ይህ እርምጃ የተወሰደው በአቶ አሰፋ ማሩ መገደል ከኢትዮጵያ መንግሥት ለጠየቁት ማብራሪያ ምንም አጥጋቢ መልስ ባለማግኘታቸው መሆኑን ገልጸው ለወደፊቱም በአዲሱ ፖሊሲ መመሪያ መሠረት ከማንኛውም መንግሥት ጋር ብሪታንያ በምታደርገው ግንኙነት "ለሰው ልጅ መብት መከበር ከፍተኛ ቅድሚያ የምንሰጥ ይሆናል" በማለት በይፋ አስታውቀው ነበር።

ባለፈው ሳምንት ይህንኑ አዲስ ፖሊሲ በማስፋፋት የውጭ ተራድኦ ሚኒስቴሩ የተከበሩ ክሌር ሾርት ለፓርላሜንት ንግግር ባደረጉ ማግሥት እዚያው በዚያው ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ካሉ በሰው ልጅ መብት ረገጣ እንደጉድ መታየት የጀመሩ መንግሥታትን ፖሊስ ለማሰልጠን ሌላ ውል መፈረሙን አደናጋሪ የሆነ ቅራኔ እንደሆነ ማንም የሚስተው አይመስለንም። በ 7 ኖቬምበር የወጣው ዘ ጋርድዲያን የተባለው የለንደን ጋዜጣ በዚሁ ጉዳይ ሲተች "አዲሱ የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ፖሊሲ ተብሎ የተገለጸው መመሪያ ኢትዮጵያን አስመልክቶ በተወሰደው እርምጃ መፍረክረክ መጀመሩን" በመገረም አውስቷል።

የእንግሊዝ መንግሥት እንደተለመደው የራሴን ብሄራዊ ጥቅም ማስከበር እንጂ የሰብአዊ መብት ጉዳይ አያገባኝም ብሎ በግልጽ ተናግሮ ይህንን ግፈኛ ፖሊስ ማሰልጠንና ማጠናከሩን ቢቀጥል ኖሮ ምንም አይገርመንም ነበር። ግን ደግሞ አዲስ የሰው ልጅ መብትን የሚያራምድ ፖሊሲ ወጣ እየተባለ እየተለፈፈ እዚያው በዚያው መንፈቅ ሳይሞላ አቋምን መቀልበስ ብዙ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው። ከአህአደግ ጋር የፖሊስ ትብብር እንደገና የጀመረው፤ ይህ ግፈኛ መንግሥት ከዛሬ 6 ወር ይልቅ ይበልጥ የሰው ልጅ መብት አክባሪ ሆኖ ነው? ወይስ የሰው ልጅ መብት ሲባል እኛን ኢትዮጵያውያንን አይጨምርም? ? እንዲህ አይነቱ ችግር ውስጥ ከመግባት አዲሱ የእንግሊዝ መንግሥት ስለ አዲስ የሰው ልጅ መብት የሚያከብር የውጭ ፖሊሲው ሃተታ ቢያጠብ ወይ ደግሞ አዲሱ ፖሊሲው ህዝቦችን ሁሉ በእኩል አይን የሚያይበት ጽናት ቢኖረው ይመረጥ ነበር። ለዚህ ነው ጥንቱን ባልዘፈንሽ ፤ ከዘፈንሽ ባላሳፈርሽ ያልነው////